# ግንቢት ሰባት - ዳግምዊ ኢሕአፓ ነዉን ?
# አማኑዔል ዘሰላም

ጁላይ 25 2008

“ዶ/ር ብርሃኑ ጠመንጃ አወጁ ይባላል። እዉነት ነዉ እንዴ ?” ብሎ አንድ ወዳጄ ደዉሎ ጠየቀኝ። ለመመለስ ትንሽ አንገራገርኩኝ። ዘግየት የማለትና የማቅማማት ነገር ታየብኝ። የምመልሰዉን አላወኩም ነበር። መሃል መሃል እያረፍኩኝ ዶ/ር ብርሃኑ ከቅንጅት እንደወጡ፣ በአሁኑ ሰዓት በዉጭ አገር እንደሚኖሩ፣ ግንቦት ሰባት የሚባል አዲስ ድርጅት እንደመሰረቱና የጠመንጃ ትግል ይሁን ምን ይሁን የማይታወቅ የ”አመጽ ትግል” ብለዉ የሚጠሩትን ለመጀመር እንደወሰኑ ተናገርኩኝ።

ዶ/ር ብርሃኑና ሌሎች የግንቦት ሰባት መስራች የአመራር አባላት በርካታ ረጃጅም ጽሆፎችን አበርክተዋል። አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌ ባልሳሳት ባለፉት 6 ወራት ብቻ ከአምስት ያላነሱ ባለ ብዙ ጽሁፎችን ሲጽፉ፤ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ እርሳቸዉም እንደዚሁ በፊናቸዉ ሃሳባቸዉን በሰፊዉ ያስረዱበት መድረኮች አያሌ ናቸዉ።

በየሳምንቱ አንዴ የሚወጣዉ የግንቦት ሰባት እትም አሁን ቁጥር 9 ደርሷል። በዲሲ፣ በለንደን፣ በጀርመን፣ በሎስ አንጀለስ .....እንዲሁም በሌሎች በርካታ ሕዝባዊ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት የግንቦት ሰባት መሪዎች መግለጫ ሰጥተዋል። የከረንት አፌር ፓልቶክ ሩም በሚባለዉ የዉይይት መድረክ በተለያዩ ጊዚያት እየተገኙ ለሰዓታት ቃለ መጠይቆች አድርገዋል። አዲስ ድምጽ የተሰኘዉ ሬዲዮ ጣቢያም ብዙ ጊዜ እነ አቶ አንዳርጋቸዉን አቅርቦ ያነጋገረ ሲሆን በኢትዮጵያ የሚታተም አዉራምባ ታይምስ በተሰኘዉም ጋዜጣ አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌና ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ያደረጉት ቃለ መጠይቅ ሰፍሮ ለአንባቢያ ቀርቧል።

እንደዚያም ሆኖ ግን ስለ ግንቦት ሰባት በአይምሮዬ ያሉ በርካታ ጥያቄዎች ሊመለሱልኝ ገና አልቻሉም። ለምንድን ነዉ ከቅንጅት መዉጣት ያስፈለጋቸዉ ? እንዴትስ ነዉ ዉጭ አገር ተቀምጠዉ ትግል ሊመሩ የሚችሉት ? የአምጽ ትግል ሲሉ የትጥቅ ትግል ማለታቸዉ ነዉ ወይ ? የትጥቅ ትግል ማለታቸዉ ከሆነ ታዲያ የአርበኞ ግንባር ነን ብለዉ እራሳቸዉን ይጠሩ እንደነበሩትና አሁን የት እንዳሉ እንደማያታወቁት ለምን በገሃድ «የትጥቅ ትግል ለማድረግ ነው» ብለዉ አይናገሩም ? ሁለገብ ትግል ነዉ የምናደርገዉ ካሉን ደግሞ ከነኢሕአፓ በምን ይለያሉ ? እነ ኢሕአፓ ይኸዉ ከሰላሳ አመት በላይ የዳያስፖራ ፓርቲ ሆነው «እዚህ ግባ» የሚባል ዉጤት አላመጡም። ታዲያ ግንቦት ሰባት ኢሕአፓ የሚጠቀምበትን ስልት ከተጠቀመ ፣ ከኢሕአፓ የተለየ ዉጤት ያመጣል እንድንል ምን የተለየ ማጂክ አለዉ ? ለሁለ ገብ ለሁለ ግብ ትግል ከሆነ ደግሞ ኢሕአፓ እያለልኝ ወደ ግንቦት ሰባት ለምን እሄዳለሁ ? ግንቦት ሰባት የህብረትን አስፈላጊነት እየተናገረ አብረዋቸዉ ከነበሩ ከቅንጅት ሰዎች ተለይተዉና በዉጭ አገር ካሉት የድጋፍ ድርጅቶች ጋር ተቃቅረዉ ባሉበት ሁኔታ እንዴት ተደርጎ ነዉ የፖለቲካ ድርጅቶችን አብሮ ለማምጣታት የሞራል ብቃት የሚኖራቸዉ ?..እነዚህንና የመሳሰሉ ብዙ ጥያቄዎች ነበሩኝ።

በአይሞሮዬ ለሚመላለሱ ለዚህ ጥያቄዎች መልስ አገኝ እንደሆን ብዬ በቅርብ አቶ አንዳርጋቸዉ በብዙ ድህረ ገጾች ላይ የበተኑትን ጽሁፍ አግንቼ ደጋግሜ አነበብኩኝ። ይህ ጽሁፍ አቶ አንዳርጋቸዉ በሎስ አንጀለስ የግንቦት ሰባት ፓርቲ ባዘጋጀዉ ስብሰባ ላይ ያቀረቡትን ንግግር የያዘ ጽሁፍ ነዉ።

ከዚህ በፊት ከቀረቡ ማብራሪያዎች ትንሽ የተሻለ ግልጽነትን ጽሁፉ ላይ አይቼበታለሁኝ። በተለይም ግንቦት ሰባት ሊያራምዳቸዉ ስላሰባቸዉ የትግል አማራጮች ዘርዘር ባለ መልኩ ቀርበዋል። በጹሁፋቸዉ መደምደሚያ ላይም ፣ አቶ አንዳርጋቸዉ፣ ኢትዮጵያዉያን ወደ ድህረ-ገጻቸዉ ሄደዉ የግንቦት ሰባት አባል እንዲሆኑ ጥሪ አቅርበዋል።

አቶ አንዳርጋቸዉ ጽሁፍ ላይ ያለኝን አስተያየት በዝርዝር ከማቅረቤ በፊት ለአቶ አንዳርጋቸዉ የአባልነት ጥሪ ቀጥተኛና ግልጽ ምላሽ መስጠት እፈልጋለሁኝ።"ስለ ጥሪዎት አመሰግናለሁ። አባል መሆኑ ግን ይቅርብኝ" እላለሁኝ።

ይህን  የግሌ የሆነ ነጻ አስተያየት ሳቀርብ የአቶ አንዳርጋቸዉን ጽሁፍ ያወጡ ድህረ ገጾች የኔንም እንደሚያወጡልኝና እነ አቶ አንዳርጋቸዉም "ወያኔ" እንደማይሉኝ ተስፋ እያደረኩኝ ነዉ። ይህን የጻፍኩት በግለሰበ ደረጃ የግንቦት 7 መሥራቾቹ ላይ ችግር ስላለኝ አይደለም። አብዛኞቹ ከዚህ በፊት ያደረጉትን አስተዋጾ የማከብርና ለከፈሉትም መስዋዕትነት ትልቅ ቦታ የምሰጥ ሰዉ ነኝ። በዚህ አጋጣሚ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዉያን ስለከፈሉት መስዋእትነት እንደ ኢትዮጵያዊ «እግዚአብሄር ይስጥልኝ» እላለሁኝ።

ግንቢት ስባትን ሆነ ድርጅቱ የሚያራምደዉን ፖለቲካ ስቃወም ግልጽ ዉይይት ማድረጉ፣ መወቃቀሱ ለዲሞክራሲ ባህል መጎልበት ይጠቅማል ከሚል አንጻር ነዉ የተነሳሁት።ያለመከልከልና ያለፍርሃትም  ሃሳቤን የምገልጸዉ ለዚሁ ነዉ።

## <u>ግንቦት ሰባት እና ተጠያቂነት</u>

ግንቦት ሰባት እንደ ኢሕአፓ በሚስጥር የተደራጀ፣ በሚስጥር የሚንቀሳቀስና በሚስጥር የሚሰራ ድርጅት ነዉ። የአመራር አባላቱ ቀን ቀን የቅንጅት ደጋፊ ሆነዉ በቅንጅት ስም በየከተማዉ ሲዞሩ፣ ማታ ማታ ደግሞ የግንቦት ሰባትን መረብ ሲዘረጉና አባላትን በሚስጥር ሲመለምሉ ቆይተዋል።

ዶ/ር ብርሃኑና ጓደኞቻቸዉ የሚታወቁት በሰላማዊነታቸዉ ነበር። በአጭር ጊዜ ዉስጥ ከግራ ወደ ቀኝ መዞራቸዉ በርካታ ደጋፊዎቻቸዉን አስደንግጧል። ያኔም ጦረኝነት በዉስጣቸዉ እንደነበረና ድርብ ማንነት (ደብል ፐርሰናሊትይ) ይዘዉ ይንቀሳቀሱ እንደነበረ ብዙዎች ይገምታሉ።ትላንት የሰላም ሃዋሪያ የነበሩ ዛሬ ጦረኛ ከመቀሰፈት አይሆንምና።

እንግዲህ ይህ ሁሉ ዉስጣዊ ሥራ ሲሰራ በርካታ የቀድሞ የቅርብ ጓደኞቻቸዉና ደጋፊዎቻቸዉ ሳያዉቁት ነበር በሚስጥር ሲሰራ የነበረዉ።

ይህ ሚስጥራዊ አሰራር የሚያስከትላቸዉ መሰረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች አሉ። ከነዚህ ዋናዉ የተጠያቂነት ጥያቄ ነዉ ? የግንቦት ሰባት ድርጅት ዲሞክራሲያዊ ነዉ ወይ ? አመራሩ ዲሞክራሲን የሚለማመድ ነዉ ወይ ? እንዴት ነዉ ጥፋት ካጠፉ ወይንም ገንዘብ ከባከነ አመራሩን ተጠያቂ የምናደርገዉ ? አሁን ያሉት የአመራር አባላት የእድሜ ልክ መሪዎች ናቸዉ ወይ ? (ከሰላሳ አመታት በላይ እነ ዶ/ር ነገ ጎበዜ  እነ አቶ እያሱ አለማየሁ የድርጅቶቻቸዉ መሪ እንደሆኑት ማለት ነዉ)

እዚህ ላይ ግንቦት ሰባት የተጠያቂነት ችግር ያለበት እንደሆነ እናያለን። «እኛን እመኑን። የኛ አማራጭ ትግል ለዉጥ ያመጣል» እያሉን ነው። ይህ ትልቅ ስህተት አድርጌ አየዋለሁኝ። በተለይም እንደነ አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌ አይነቱ፣ መሪዎች ተጠያቂ ካልሆኑ ሊያስከተለዉ የሚችለዉን ችግር ያዩ፣ እንደዉ በጭፍኑ «እርዱን ደግፉን» ማለት ቢቀል የዋህነት ቢብስ ድርቅና እንደሆነ የሚያጡት አይመስለኝም።

በገጽ አንድ ላይ አቶ አንዳርጋቸዉ ሲጽፉ «የግንቦት ሰባት አባላትም ለረባዉና ላልረባዉ መልስ በመስጠት በፖለቲካዉ ዉስጥ ለሚነሳዉ መከራከርና ይህ ለሚቀሰቅሰዉ ምሬት፣ ምሬቱ ለሚፈጥረዉ ሕሊና መሳት፤ ህሊና ስቶ ለሚከተለዉ ብልግና አጋፋሪ የመሆን ፍላጎት የላቸዉም" ብለዋል።

እርግጥ ነዉ ለአልባሌ እንካ ሰላምታዎች ጊዜና ቦታ መስጠት አይገባም። ነገር ግን ከሕዝቡ የሚነሱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ተቃዉሞዎች ሊቀርቡ ይችላሉ። ግንቦት ሰባት፣ ጥያቄዎችን አጣጥሎ ከሚያልፍ በግልጽና በሰለጠነ መልኩ ዉይይቶችን ቢቀላቀል መልካም ነዉ እላለሁኝ። ሰበብ እየሰጡ እኛ ሚስጥራዊ ነን

እያሉ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን አለመመለስ የበለጠ ሌሎች ጥያቄዎችን የሚፈጥርና ለግንቦት ሰባት የማይበጅ እንደሆነ ነው የሚገባኝ።

ግልጽነት፣ ተጠያቂነት ዲሞክራሲያዊነትን ያላካተተ በሚስጥርና ዉስጥ ዉስጡን የሚሰራ ድርጅት ብዙ አይጥመኝም። እርግጥ ነዉ በኢትዮጵያ በሕዕቡ መደራጀት ከተፈለገ ኢትዮጵያ ያሉ አባላት መታወቅ የለባቸዉም። (ለደህንነታቸዉ ሲባል) እርሱ ይገባኛል። ነገር ግን በዉጭ ያለዉ እንቅስቃሴ ቢያንስ ቢያንስ ግልጽና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መልኩ መደራጀት ነበረበት ። አቶ ሙሉነህ እዮዔል ስዊድን ላለ ሬዲዮ እንደገለጹት የግንቦት ሰባት አባላት በቁጥር ብቻ መታወቅ የለባቸዉም። ሶስት ወይንም አራት ሰዎች ተሰብስበዉ «ደግፉን ፣እርዱን» ብለዉ ሲነሱ ያለአንዳች ማቅማማት፣ ያለአንዳች ማጣራትና ያለአንዳች ጥያቄ መርዳት ካለፈዉ ስህተተ አለመማር ይመስለኛል።

## ግንቦት ሰባትና ወያኔ-ኢሕአዴግ

አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌ በጽሁፋቸዉ አስፍረዉታል። በበርካታ የግንቦት ሰባት ደጋፊዎች ዘንድ የሚንጸባረቅ ፍጹም የተሳሳተ አመለካከት ነዉ። “አንድን ነገር ወያኔ ከደገፈዉ መጥፎ መሆን አለበት፤ ወያኔ ደግሞ ከተቃወመዉ ጥሩ መሆን አለበት” የሚለዉ አባባልና አመለካከት።

«የወያኔ የሜዲያ አዉታሮች ግንቦት 7ን የጥቃት አላማቸዉ አድርገዉ መንቀሳቀሳቸዉ ግንቦት 7ን ጥሩ ሥራ እየሰራ ለመሆኑ ማስረጃ ነዉ» ሲሉ ነበር አቶ አንዳርጋቸዉ የገለጹት። በርሳቸዉ አባባል ትግል የሚለካዉ ወያኔ-ኢሕአዴግ በሚናገረዉ መሆኑ ነዉ። ሲቀጥሉም «ሊያሳስበንና ሊያስጨንቀን ይገባ የነበረዉ የምንለዉን ነገር ትክክለኛነት ተቀብለዉ የወያኔ ኢሕአዴግ የሜዲያ ተቋማት ቢያስተጋቡ ነበር” በማለት በወያኔ-ደገፊ ሜዲያዎች አንድ ነገር ከተዘገበ መጥፎ እንደሆነ አድርገዉ ያቀረቡት።

ይህ የአቶ አንዳርጋቸዉ ሎጂክ በጣም የተሳሳተና ጨለምተኝነት የሞላበት ሎጂክ ይመስለኛል። አቶ አንዳርጋቸዉ አቶ አንዳርጋቸዉ የሆኑት አቶ አንዳርጋቸዉ በመሆናቸዉ ነዉ። ወያኔ ነገ ተነስቶ «አቶ በለጠ» ቢላቸዉ አቶ በለጠ አይሆኑም። ድመት ድመት ናት። ዉሻም ዉሻ ነዉ። አምበሳ ወያኔ ስላለ ነብር አይሆንም። እባብ ደግሞ እግር አዉጥቶ አይንቀሳቀስም።

እንደዚሁም በተመሳሳይ ሁኔታ መጥፎ ሥራ መጥፎ ሥራ ነዉ። ጥሩ ሥራ ደግሞ ጥሩ ሥራ ነዉ። ወያኔ ስለደገፈ ጥሩ ስራ መጥፎ ስራ፣ ጥሩ ሃሳባ መጥፎ ሃሳብ አይሆንም። ወይንም ወያኔ ስለተቃወመዉ መጥፉ ስራ ጥሩ ስራ፣ መጥፎ ሃሳብ ጥሩ ሃሳብ አይሆንም።

አንድ ነገር መለካት ያለበት በይዘቱና በዉስጡ ባካተተዉ ነገር እንጂ ሰዎች በሚሉት ሊሆን አይገባም። መቼም ሁላችንም ማመዛዘንና መመርመር የምንችል ይመስለኛል። ያለዉን ተጨባጭ ሁኔታ ግንዛቤ ዉስጥ በመከተት «ይህ አያዋጣም። ይህ ያዋጣል። ይህ መጥፎ ነዉ፤ ይህ ጥሩ ነዉ» የማለት አቅም ይኖረናል ብዬ አስባለሁ።

## ግንቦት ሰባትና ሪፖርተር ጋዜጣ

ሪፖርተር ጋዜጣ በተለይም የቅንጅት መሪዎች፣ ጋዜጠኞችና ሰባዓዊ ሙብት ተከራካሪዎች እሥር ቤት በነበሩበት ወቅት ጊዜ ያትማቸዉ የነበሩት ጽሁፎች በጣም አሳፋሪና አሳዛኝ ነበሩ። ይህ ጋዜጣ ሌሎች ጋዜጦች ሲዘጉና አዛጋጆቻቸዉም ሲታሰሩ ለሥራ ባልደረቦቻቸዉ ሲቆም አላየንም። ጋዜጠኞች እንዲፈቱ ሲታገል አላየንም። በኢሕአዴግ የተሰራዉን ግፍ ሲያወግዝ አላየንም። ይህ የሪፖርተር ጋዜጣ በፈታኝ ወቅት ሃላፊነቱን የጣል አሳፋሪ ጋዜጣ እንደነበረ እኔም ሆነ አብዛኛዉ ኢትዮጵያዉ ጠንቅቀን የምናዉቀዉ ጉዳይ ነው።

አቶ አንዳርጋቸው ይህንን ጋዜጣ እንደወያኔ ወንድም አድርገዉ መቁጠራቸዉ በመጠኑ ይገብኛል። ነገር ግን ይህ ጋዜጣ በአሁኑ ወቅት ወደ መልካም መስመር እየመጣ ያለ እንደሆነ መዘንጋት የሚኖርባቸዉ አይመስለኝም። ባለፈዉ የተደረገዉን አሳፋሪ የክልል ምርጫ ሪፖርተር አሳዛኝ እንደሆነ አትሟል። የአዲሱን የፕረስ ሕግ አዉግዟል። በየጊዜዉም ኢትዮጵያ ዉስጥ ሰላማዊ በሆነ መንገድ እየተንቀሳቀሱ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች ቃለ መጠይቆችን አስፍሯል።

አንድ ተቋም ማሻሻል ሲያደርግ ሊበረታታ ይገባል። ወገናዊ የነበረ ጋዜጣ ዲሞክራሲያዊ አሰራርን ማስተናገድ ሲጀምር፣ የአምባገነን ገዢ ፓርቲ አካል የሆኑ ግለሰቦች ከአምባገነንነት የወጣ መጠነኛ መሻሻል ሲታይባቸዉ .....ወደ መልካሙ ጎዳና ጉዚ ሲጀመር ሊበረታታና ሊደገፍ ነዉ እንጂ የሚገባዉ ሊኮነን አይገባም ባይ ነኝ።

የሚበጀዉ ሪፖርተር ጋዜጣ ያለፈዉን ስህተት እንዳይደግም የፈለገ ማዕበል ቢመጣ ለዲሞርክራሲና ለህዝብ እንዲቆም አምባገነንነትንም የበለጠ እንዲታገል ማበረታት ያስፈልጋል።

<u>**አራቱ የትግል አይነቶች**</u>

አቶ አንዳርጋቸዉ በጽሁፋቸዉ ሊደረጉ የሚችሉትን የትግል አይነቶች በአራት ከፍለዉ አስቀምጥዋቸዋል። እነርሱም ሰላማዊና ሕጋዊ የሆነ፣ ሰላማዊና ሕጋዊ ያልሆነ፣ ሰላማዊ ሆኖ ሕጋዊ ያልሆነና ሕጋዊ ያልሆነ ግን ሰላማዊና አመጽን ያጣመረ ትግል ናቸዉ። እዚህ ላይ ሕጋዊ ሲሉ ሕገ-መግስቱን ወያንም አለም አቀፍ ሕግን ያከበረ ማለታቸዉ አይመስለኝም፤ ነገር ግን ኢሕአዴግ የሚቆጣጠረዉ ፓርላማ የሚያወጣዉን ሕግ ተብዬ ሕግን ማክበርን እንጂ።

ሰላማዊና ሕጋዊ ያልሆነ ትግል ብለዉ ያስቀመጡት ሙሉ ለሙሉ የትጥቅ ትግል እንደሆነ አቶ አንዳርጋቸዉ አስረድተዉ፤ ግንቦት ሰባት በአራተኛነት ያስቀመጡትን ሕጋዊ ያልሆነ ነገር ግን ሰላማዊና አመጽን ያጣመረ ትግል እንደሚቀበል ገልጸዋል።

መቼም አንዳንዶቻቹ ይህን ሃሳብ ለመጨበጥ ይከብዳቹህ ይሆናል። አዎ ትንሽ የተወሳሰበ ነዉ። ይህ ሲተነትኑት ዉስብስብ የሆነው የትግል ስልት ሰላማዊ ግን ህጋዊ ካልሆነዉና ሰላማዊም ሕጋዊም ካልሆነዉ ትግል መካከል ያለ የትግል ስልት ነዉ።

ሰላማዊ ሆኖ ግን ሕጋዊ ያልሆነዉ ትግል አቶ አንዳርጋቸዉ «ሕጋዊ አይደለም» አሉት እንጂ እኔ የአለም አቀፍን ሕግ ያልጣሰ ሁሉ (የወያኔ -ኢሕአዴግንም ሕግ ቢጥስም) ሕጋዊ ትግል አድርጌ ነዉ የማየዉ። ይህ ትግል ሰዉን በማጥፋት ላይና ጥያት በመተኮስ ላይ ያተኮረ ትግል አይደለም። ነገር ግን በሕቡዕ መደራጀትንና ዉስጥ ዉስጡን ሕዝብን ማደራጀትን ይጠይቃል። ከፍተኛ መስዋዕትነትን የሚያስከትልና ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ያልተሞከረ ትግል ነዉ። ይህ ትግል አይሰራም ወይንም አልሰራም ማለት አይቻልም። ለምን ? አልተሞከረምና።

በርካታ ኢትዮጵያዉያን ግንቦት ሰባት ይህን አይነት ትግል ለማድረግ የተዘጋጀ ነበር የመሰላቸዉ። ግንቦት ሰባት ታጣቂዎች አይኖሩትም፣ ሰላማዊ ትግልን ነዉ የሚቀበለዉ፤ ነገር ግን ወያኔን እያስፈቀደ ትግሉን አያደርግም" እያሉ ነበር አንዳንድ የግንቦት ሰባት ደጋፊዎች የሚናገሩት።

በዚህ ጽሁፍ ግን አቶ አንዳርጋቸዉ እንዳስቀመጡት ግንቦት ሰባት ይህን "ሰላማዊ ግን ሕጋዊ ያልሆነን" ትግል አይደለም ሊጠቀም ያሰበዉ።

አቶ አንዳርጋቸው ስለዚህ ሰላማዊ ግን ህጋዊ ያልሆነ ትግል ሲናገሩ «በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ በድብቅና በሕብኡ የሚደራጀዉ ሰላማዊ ትግል **ራሱን ለመከላከል የሚችልበትን አቅም ማዳበር ይኖርበታል።** ይህ የመከላከል አቅም ለሰላማዊ ትግል አድራጊዉ ህዝብ የልብ ልብ እንዲሰማዉ የሚያደርግ፣ ሊያፍኑት የሚፈልጉትም እንደለመዱት በማን አለብኝነት እየተነሱ ያለምንም ፍራቻና የአጸፋ ጥቃት ሕጻናትና እናቶች እየጨፈጨፈ መኖር የሚችሉበት

ሁኔታ አለመኖሩን በማሳየት ከእብሪታቸዉ ትንሽም ቢሆን እንዲታቀቡ ማድረግ መሆን አለበት ብለን እናምናለን" ነበር ያሉት።

በሌላ አባባል ግንቦት ሰባት ራስቸዉን ለመከላከል የታጠቁ ኃይላት ይኖሩታል ማለት ነዉ። ራስን በመከላከል ሂደትም ከኢሕአዴግ የደህንነት አባላት ጋር የተኩስ ልዉዉጥ ሊፈጠር እንደሚችልም የታወቀ ነዉ። ወደ ሌላ ፍልስፍና ሳንገባ የእርስ በርስ ጦርነት ተስፋፋ ማለት ነዉ።

እዚህ ላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ግፍ መሮት ቢሸፍትና ነፍጥ ቢያነሳ እኔ ከዉጭ አገር ተቀምጬ ለምን ማለት አልችልም። የሞራል ብቃትም የለኝም። ነገር ግን ሕዝባችን መሮት ወደ ከፋዉ ደረጃ እንዳይሄድ በሰላምና በንግግር የአገራችን ችግር በቶሎ እንዲፈታ ሁላችንም ያለ የሌለ አቅማችንና ጉልበታችንን ማፍሰስ አለብን እላለሁኝ። "ሰላም ሰላም ፣ እርቅ እርቅ" ስንል አማራጩ እጅግ በጣም የከፋ እንደሆነ በመጬነቅ ነዉ። አንዳንዶች ወያኔ ይለማመጣሉ ይሉናል። አቶ መልስ እግር ስር ወድቀን አገራችን ከደም መፋሰስ የምትድን ከሆነች እግር ስር እንወድቃለን። ሰዉ ለአገሩ ይሰዋ የለም እንዴ ? ለጥቂት ሰሞን ክብራችን ቢነካ ምን እንሆናለን ?

በተለይም ሕዝባችን እጅግ በመረረዉ ወቅት፣ ጫፍ ላይ በደረሰበት ወቅት የጦርነትንና የትጥቅን ከበሮ ዉጭ ተቀምጦ መምታት ነዳጅ በሞላበት ቤት ዉስጥ ክብሪት እንደመጫር አድርጌ ነው የማየዉ። ማባባሳችንን አቁመን ለሕዝባችን የሚጠቀመዉን ሰላማዊ የፐለቲካ ትግል አምድረጉ ይበጃል እላለሁኝ።

እስቲ አንድ ሊሆን የሚችል ሴናሪዮ ላስቀምጥ። በአንዲት ከተማ የአጋዚ ጦር ወጣቶችን ማሰር ይጀምራል። ከዚያ የታጠቁ የግንቦት ሰባት አባላት አንድ አሥር አጋዚ ይገድላሉ። የሞቱትን የአጋዚ ወታደሮች ኢሕአዴግ በሽብርተኞች ተገደሉ ብሎ መግለጫ ያወጣል። ለአለም አቀፉ ሕብረ ተሰብ ያሳወቃል። ሁለት ሳምንት ቆይቶ ያለ የሌለ ኃይሉን ይጠቀምና በዚያ ከተማ ያሉትን የአንድነት የሕብረት የመኢአድ ... ደጋፊዎች ሁሉ ሳይቀር ግንቦት ሰባት ናችሁ እያለ ይመታል።

የጦርነት ሜዳ ስለሆነ በሰላማዊ ትግል እንደሚሞተዉ ሰዉ አለም አይንጫጫም። ሽብርተኞችን እየመነጠርኩኝ ነዉ ይላል ኢሕአዴግ። እንግዲህ በዚህ ወቅት የግንቦት ሰባት ታጣቂዎች ሕዝቡን ከማስጨረስና ለወያኔ-ኢሕአዴግ ህዝቡን እንዲመታ ምክንያት ከመሆን ውጭ የሚያመጡት ምን ፋይዳ አለ ? ሕዝቡን ነጻ አዉጥተዉ ነጻዉን መሬት መከላከል ቢችሉ ኖሮ እርሱ ሌላ ጉዳይ ነዉ። ነገር ግን ያንን ማድረግ አይችሉም። ለምን አቶ አንዳርጋቸዉ ሲናገሩ ሕጋዊና ሰላማዊ ያልሆነ ሙሉ ለሙሉ የትጥቅ ትግል የሚጠይቅ የትግል ስልት አይቀበሉም።

ተመልከቱ በምዕራቡ የአገራችን ክፍል የሆነዉን። የኦፌዲን (የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ) እንዲሁም ዶ/ር መራራ ጉዲና የሚመሩት ድርጅት አባል የሆኑት ኢትዮጵያዉያን ኦነግ ሳይሆኑ "ኦነግ" ናችሁ እየተባሉ ብዙዎቹ ታስረዋል። የኦነግ በዚያ አካባቢ የዉትድርና እንቅስቃሴ ማድረግ ሕዝብን ነጻ አላወጣም። ህዝብን የበለጠ አደጋ ላይ ጣለ እንጂ።

አቶ አንዳርጋቸዉ ያቀረቡልን አማራጭ እንግዲህ ይህ ነዉ። የማይሰራ፣ አገራችንን እጀግ ወደ ከፋ ሁኔታ ላይ የሚወስድ፣ ወያኔ-ኢሕአዴግን የሚያጠናክርና የበለጠ ህዝቡን ለማፈን ሰበብ የሚሰጠዉ፣ ከሰላሳ አመታት በፊት ኢሕአፓ ያደረገዉን የሚደግም የኋል ቀር ትግል ነዉ።

እኔ አጥብቄ እቃወመዋለሁ። ኢትዮጵያዉያንም ይህን ነፍጥ የመያዝን ትግል እንዲቃወሙ እመክራለሁኝ።ለኛ አይበጀምንም። ለኢትዮጵይ አይበጃትም።

ህዝብን በሕብሉ ማደራጀቱ ከሆነ፣ ሕዝብን በራሱ እንዲተማመን ማስተማሩ ከሆነ፣ ህዝብን ለመብቱና ለነጻነቱ እንዲታገል ማበረታታቱ ከሆነ የኢትዮጵያዉያንን ደም በማፍሰስ ላይ ያላተኮረ፣ የአለም አቀፍን ሕግ የጠበቀ በአብዛኛዉ ኢትዮጵያዊ የሚደገፍ ትግል ማድረግ ይቻላል። ይህም አይነት ትግል በሕዝብ ጉልበት ላይ የሚተማመን ስለሆነ ዉጤት በርግጥ ያመጣል።